# በቤልጅየም እና በኔዘርላንድስ ነዋሪ የሆናችሁ ኢትዮጵያውያን በሙሉ

**በተለያዩ ሀገራት ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት በመሳተፍ ራሳቸውንም ሆነ አገራቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ ይችሉ ዘንድ ወጥ የሆነ የዳያስፖራ ፖሊሲ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ ከዚህ በፊት የዳያስፖራውን ጥቅሞች ለማስጠበቅ የወጡ ህጎችና መመሪያዎችን እንዲሁም ተሞክሮዎችን በማካተት የዳያስፖራ ፖሊሲ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡**

**ይህ ፖሊሲ ጸድቆ ተግባራዊ መሆን ከመጀመሩ በፊት ሚስዮናችን በሚሸፍናቸው የቤኔሉክስ አገራት ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን በማወያየት ከሚኖሩበት አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በፖሊሲው ላይ ያሏችሁን አስተያየቶች ለማሰባሰብ ይቻል ዘንድ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡**

**በዚሁ መሠረት እ.ኤ.አ. ቅዳሜ ፌብሩዋሪ 18 ቀን 2012 በአንትወርፕ ከተማ ከቀኑ 14:00 እስከ 18:00 ሰዓት፤ እንዲሁም እ.ኤ.አ. ቅዳሜ ፌብሩዋሪ 25 ቀን 2012 በአምስተርዳም ከተማ በተመሳሳይ ሰዓት ስብሰባ በማካሄድ በረቂቅ ፖሊሲው ላይ ያሏችሁን አስተያየቶች ለማሰባሰብ ፤ እንዲሁም የከተማ ቦታ ይዞታን አስመልክቶ በቅርቡ በጸደቀው የሊዝ አዋጅ ላይ ማብራሪያ ለመስጠት የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡፡**

**በመሆኑም ኢትዮጵያዊያን በሙሉ በውይይቶቹ ላይ እንድትሳተፉ በአክብሮት እየጋበዝን፤ ረቂቁን በቅድሚያ በማንበብ ቢካተቱ ይጠቅማሉ የምትሉዋቸውን አስተያየቶች ለማዘጋጀት ይረዳ ዘንድ የፖሊሲው ረቂቅ ሰነድ በሚሲዮኑ ዌብሳይት የተቀመጠ መሆኑን እንገልጻለን፡፡**

በተጨማሪም በዕለቱ ስብሰባው በሚሄድበት ሥፍራ የህዳሴ ቦንድ ሽያጭ እና የኮንሱላር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## አድራሻ:

1. በአንትወርፕ ለሚካሄደው ስብሰባ

    National Straat 111
    2000 Antwerp

ከክፍያ ነጻ የመኪና ማቆሚያ የስብሰባው አዳራሽ ያለበት ጊቢ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን እንገልጻለን፡፡ (አንትወርፕ)

2. በአምስተርዳም ለሚካሄደው ስብሰባ

    Linnaeusstraat 37, 1093 EG, Amsterda

በህዝብ ትራንስፖርት ወደስፍራው ለመድረስ ከሴንትራል ስቴሽን የምትነሳዋን 9 ቁጥር ትራም ይዘው 1**e v. Swindenstraat (Eerste van Swindenstraat)** መቆሚያ ይውረዱ፡፡ አዳራሹን ፊት ለፊትዎ ያገኙታል፡፡ (አምስተርዳም)